# ጽንፈኞችና የህዝበ ሙስሊሙ ምላሽ!

ሲኢድ መሐመድ 8/7/12

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገራችን የመነጋገሪያ አጀንዳዎች ከሆኑ ዓበይት ጉዳዮች መካከል አንዱ በሃይማኖት ሽፋን እየተካሄደ ያለው የጽንፈኝነት እንቅስቃሴ ነው። ድብቅ የፖለቲካ አጀንዳን ለማሳካትና ለዘመናት የዘለቀውን አብሮነትና ሃይማኖታዊ መቻቻልን ለማደብዘዝ ከዚያም አልፎ የእርስ በርስ ግጭትን ለማንገስ ያለሙ ጽንፈኛ ቡድኖች ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ማድረጋቸው ነው።

የህዝበ ሙስሊሙን ድጋፍ ለማግኘት የተንቀሳቀሱ ጽፈኞች የእስልምና ሃይማኖት ለምድ ለብሰው ከእስልምና ሃይማኖት አማኞች ጋር መስለው በመቀላቀል ውስጥ ውስጡን ድብቅ አጀንዳቸውን ለማሳካት መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ ማድረጋቸው ነው። የጽንፈኞቹን አካሄድ በውል ባለመረዳት ለተወሰነ ጊዜ የሚሉትን መስማት የቻሉ የተወሰኑ የህዝበ ሙስሊሙ አባላት አልነበሩም ማለት ባይቻልም አብዛኛው የእምነቱ ተከታይ ግን በእምነት ስፍራ የሚፈጽሙትን ሃይማኖታዊ ተልእኮ ያፈነገጠ ተግባር እየተገነዘበ የቆየበት ሁኔታ ነበር። ጽንፈኞቹ "የህዝበ ሙስሊሙ ጥያቄ" በሚል ሰበብ የግል አጀንዳቸውን ለማሳካት የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት እንዲፈጸምላቸው ጠየቁ። ካቀረቧቸው ጥያቄዎች መካከልም የሌሎች እምነቶች አስተምህሮ ይከልከልልን፤ሁሉም ኢትዮጵያዊ የእኛን እምነት ብቻ ይከተል የሚል ይገኝበታል።

እነዚህ የሃይማነኖት ለምድ የለበሱ ጽፈኞች የጠየቁት ጥያቄ የሌሎችን ነጻነትና ሕገ-መንግስታዊ መበት የሚተላለፍ መሆኑ ጠፍቷቸው አይደለም። ሕገ-መንግስቱን ለመናድ ካላቸው ፍላጎት የተነሳ እነሱ የሚከተሉትን እምነት ሌላው ላይ በሃይል ለመጫን ካላቸው እምነትና ፍላጎት የመነጨ ነው።

ለመጀመሪያ ጊዜ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችን ድጋፍ ለማግኘት ነበር በሰፊው የተንቀሳቀሱት። የህዝበ ሙስሊሙን ድጋፍ ማግኘት እንደማይችሉ ባረጋገጡበት ወቅት በአማኞች ዘንድ የእርስ በርስ ግጭትና ብጥብጥ በመቀስቀስ ሰላምን ለማደፍረስና ጉዳዩን ከመንግስት ጋር ለማያያዝ ከፍተኛ ጥረት ማድረጋቸውን ቀጥለውበታል። በተለይ የእስልምና ሃይማኖት አማኞች እርስ በርስ በማበጣበጥ እና ከሌላ ሃይማኖት አማኞች ጋር በማጋጨት ሰላምን በማደፍረስ መንግስት ሰላምን ለማስከበር የሚያደርገው እቅስቃሴ በእስልምና ሃይማኖት ጣልቃ የገባ በማስመሰል አዛብቶ በማቅረብና ለዚሁም የተለያዩ ሃላፊነት የጎደላቸው ሚዲያዎችን በመጠቀም መጠነ ሰፊ ቅስቀሳ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

ጽንፈኞቹ ድብቅ አጀንዳቸውን ለማሳካት ያስችላል ብለው ያመኑበትን የተለያየ ዘዴ እየተጠቀሙ ከፍተኛ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ በማድረግ መንግስትንና ህዝበ ሙስሊሙን ለማለያየት ያልተገደበ ጥረት ያደርጋሉ። በዚህ መልክም ረጅም ርቀት ተጉዘዋል። ጽንፈኞቹ ህዝበ ሙስሊሙን ከመንግስት ጋር ለማጋጨት ያልፈነቀሉት ድንጋይና ያልበጠሱት ቅጠል ባይኖርም 'ስንቅና ውሸት እያደር ይቀላል' እንደሚባለው እውነታው እየተገለጠ መጣ። በመንግስት ጉዳይና ሃላፊነት ላይ ጣልቃ እየገቡ ያሉት ጽንፈኞቹ እንጂ መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ የገባበት ሁኔታ እንደሌለ በግላጭ ታየ። የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችም ሐቁን እየተገነዘቡ መጡ።

ከእንቅስቃሴው በስተጀርባ ግን ቀደም ሲል የተለያየ የሽብር ተግባራትን ለመፈጸም ሙከራ አድረገው የከሸፈባቸው ግንቦት 7 የተባለው አሸባሪው ቡድን፣ የኤርትራ መንግስትና "ስደተኛው ሲኖደስ" ይገኙበታል። እነዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች ባገኙት ማንኛውም አጋጣሚ በህዝበ ሙስሊሙ መካከል የተፈጠረውን ችግር ከማባባስ አልፈው ችግሩን ለሚፈጥሩ ጽንፈኞች ከፍተኛ መዋእለ ንዋይ መድበው እየሰሩ ነው፡፡

"ስደተኛው ሲኖዶስ" የኢትዮጵያ መንግስት በእስልምና ሃይማኖት ጣልቃ ገብቷል የሚል የሃሰት መግለጫ አወጣ። በቀጣይነትም ፕሮፖጋንዳ ጀመረ። የተቀደሰውን ቤተክርስቲያን ለሃይማኖታዊ ተልእኮ ማዋል ሲገባው የፖለቲካ ስብከት መድረክ አደረገው። ህዝበ ክርስቲያኑ ሃይማኖታዊ ተግባራትን ለመፈጸም በሚሰበሰብበት ወቅት የግንቦት 7 ፖለቲከኞችን እየጋበዘ በኢትዮጵያ አንድነትና ሰላም ላይ ሰፊ ዘመቻ ማድረጉን ተያያዘው። ግንቦት 7 የተባለው አሸባሪ ቡድን በበኩሉ ጽንፈኞችን በገንዘብ ከመደገፍ አልፎ ኢሳት በተባለው የየቴሌቪዥን ጣቢያው አማካይነት ያለሆነውን ሆነ ያልተፈጠረውን ተፈጠረ እያለ አጋኖ በመዘገብ ህዝብን የማደናገር አጀንዳ ይዞ በከፍተኛ ደረጃ ተንቀሳቀሰ።

በእስልምና ሃይማኖት ሽፋን የሚንቀሳቀሱ የከሰሩ ጽንፈኛ ፖለቲከኞች ከኢሳት በተጨማሪ ሰለፊያ፣ ሰውትል እስላምና ሌሎች ሃላፊነት የጎደላቸው ዓለምአቀፍና የአገር ውስጥ ሚዲያዎችን በመጠቀም በመንግስትና በህዝበ ሙስሊሙ መካከል ክፍተትና መቃቃርን ለመፍጠር ያላሰለሰ ጥረት አደረጉ። በዚህ መልክ ድብቅ የፖለቲካ ዓላማቸውን ለማሳካት ጥረት ቢያደርጉም መላው የኢትጵያ የእስልምና ሃይማኖት አማኞች ግን እኩይ ምግባራቸውን የሚያጋልጥበት አስራ አንደኛው ሰዓት ላይ ደርሷል። የተመኙትና ያቀዱት አልተሳካም፤ መንግስትና ህዝበ ሙስሊሙ እጅና ጓንት ሆነው መስራት ጀምረዋል።

በሃይማኖት ሽፋን የሚንቀሳቀሰው አክራሪ ቡድን እንቅስቃሴ ከጀመረ ረጅም ጊዜ አድርጓል። በአንዳንድ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ያለው ትችት መንግስት ዘግይቷል ከመጀመሪያ ጀምሮ እርምጃ መውሰድ ይገባው ነበር የሚል ነው። ይሁንና መንግስት በተለያየ ጊዜ ጽንፈኛው ቡድን ከእኩይ ምግባሩ ታቅቦ በሰላማዊ መንገድ ሃይማኖታዊ ተልእኮውን እንዲፈጽም ሲያሳስብ ቆይቷል።

ማሳሰቢያው ግን ያስገኘው ምንም ዓይነት ውጤት አልነበረም። ጽንፈኞች ይባሱን በሃይልና በአመጽ ፍላጎታቸውን ለማሳካት የሚችሉ መስሎ ስለተሰማቸው ለሁከት ተንቀሳቅሰዋል።

መቋጫ የሌለው የእርስ በርስ ግጭትን በመፍጠር የአገሪቱን ሰላም በማደፍረስ መንግስት ሰላምን ለማስፈንና ሕግን ለማስከበር ሊወስድ የሚችለውን እርምጃ ከሃይማኖት ጣልቃ ገብነት ጋር በማያያዝ ከህዝበ ሙስሊሙ እና ከልማት አጋሮቹ ጋር ለማቃቃር ያደረጉት የተቀናጀ ጥረትም መና ቀርቷል። በርግጥ በተደረገው የአሸባሪዎች እንቅስቃሴ የተታለሉ የሙስሊሙ ሕብረተሰብ አባላት የሉም ማለት አይቻልም። ቁጥራቸው ቀላል የማይባል የእስልምና ሃይማኖት አማኞች የእነዚህ ሰዎች አመጣጥ ከአላህ ዘንድ መስሏቸው የተወሰነ ርቀት ሊከተሏቸው ችለዋል፡፡ ይሁን እንጂ አካሄዳቸውን በውል እየተገነዘቡ በመምጣታቸው ሃይማኖታዊ ተልእኮ እንደሌላቸው በማረጋገጣቸው አብዛኛዎቹ ወደ ትክክለኛ መስመር ገብተዋል። ጥቂቶች ግን አሁንም በፍቅረ ንዋይ ማለው ከጽንፈኞቹ ጋር ለጥፋት ተሰልፈዋል። አገርን ለማፈራረስ፣ ሰላምን ለማደፍረስና ልማትን ለማደናቀፍ አልመው ለተነሱ ቡድኖች መሳሪያ ሆነዋል።

እነዚህ ፍቅረ ንዋይ ያማለላቸው የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች እምነታቸውን በገንዘብ ሸጠው ጽንፈኞቹ በሚሰጧቸው መመሪያ መሰረት ህዝቡ ሃይማኖታዊ ተልእኮውን ለመፈጸም በመስጊዶች የሚሰባሰብበትን ጊዜ እየጠበቁ ብጥብጥና ሁከት ለመፍጠር ሙከራ ሲያደርጉ ቆይተዋል። ከወሃቢያ እምነት በስተቀር ሌላ እምነት በአገሪቱ መኖር የለበትም፤ ሁሉም ሙስሊም ይህንን እምነት መከተል አለበት፤ ይህን እምነት ከሚከተል የእስልምና ሃይማኖት ውጭ ሌላ ሃይማኖት መኖር የለበትም፤ አገሪቱ በእስላማዊ መንግስት መመራት አለባት የሚሉ ጉዳዮችን ቀስ በቀስ በህዝበ ሙስሊሙ ለማስረጽና ይህንኑ ፍላጎታቸውን ሕገወጥ በሆነ መንገድ ለመፈጸም እንቅስቃስያቸውን አጠናክረው ቀጥለዋል።

ማንኛውም ሰው እነሱ የሚከተሉትን እምነት ብቻ እንዲከተል አውጀዋል፡፡ አገሪቱ የእስልምና ሃይማኖት መንግስት ሊኖራት ይገባል ሲሉም ቀላል የማይባል ዘመቻ አካሂደዋል፡፡ ይህንን ሁሉ ማድረግ የቻሉት ግን የአገሪቱ ሕገ መንግስት የሰጣቸውን በነጻነት የመሰብሰብና የፈለጉትን ሃይማኖት የመከተል መብት በመጠቀም ነው። ይህ መብት ለእነሱ ብቻ የተሰጠ ይመስል ሌሎች ላይ ተጽእኖ ለማሳደር ህጋዊ ባልሆነ መልክ ተንቀሳቅሰዋል። እንቅስቃስያቸው ስር እየሰደደ መጥቶ በአዲስ አበባ በቅርቡ የተካሄደውን 19ኛ የአፍሪካ መንግስታት ጉባኤን ለማወክ ሞክረዋል። ኢትዮጵያ የገነባችውን መልካም ገጽታ ጥላሸት ለመቀባትም ጥረዋል። እንቅስቃሴው ስብሰባውን በማወክ እንግዶችና የዓለም ሕብረተሰብ በአገሪቱ ሰላም የለም የሚል ድምዳሜ ላይ እንዲደርስ ለማድረግ ያለመ ነበር።

እንደዚህ ዓይነቱ ድርጊት አሁን ብቻ የተከሰተ አልነበረም። ቀደም ባለው ጊዜም የተለያዩ ተመሳሳይ ሙከራዎች ተደርገዋል። እነዚህን ጽንፈኞች በቀጥታ እያሰማሯቸው ባሉት የግንቦት 7 እና የኤርትራ

መንግስት ትብብር በአገሪቱ የልማት ተቋማት ላይ የቃጧቸው ጥቃቶች ከሽፈዋል። አሸባናሪዎቹም ብዙ ርቀት ሳይጓዙ በጸጥታ ሃይል ቁጥጥር ስር ውለዋል። በተመሳሳይ መልኩ የአፍሪካ መሪዎች ለስብሰባ አዲስ አበባ በገቡበትና ሌሎችም ዓለም አቀፍ ተቋማትና አጋር አገራት መንግስታት በአዲስ አበባ የአፍሪካ ሕብረት በተሰበሰቡበት ጊዜም አዲስ አበባን ባግዳድ እናደርጋታለን በሚል መፈክር የተላኩ የሻዕቢያና የግንቦት 7 ቅጥረኞች እቅዳቸውን ሳያሳኩ በህዝብና በጸጥታ ሃይል በተደረገ ክትትል ከተቀጣጣይ ፈንጂቻቸው ጋር በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ተደርጓል። ጽንፈኞቹ በቅርቡ ያደረጉት ሙከራም የዚሁ ተቀጽላ መሆኑ እሙን ነው።

በአገራችን በሃይማኖት ሽፋን በመንቀሳቀስ ላይ ያለው አክራሪ ቡድን ቀደም ሲል በተለያየ መልኩ በአገራችን ሁከት ለመፍጠር የተለያዩ ሙከራዎችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በተቀደሰው የእስልምና ሃይማኖት ስም የሚንቀሳቀሰው የዚህ ቡድን እኩይ ተግባር መላውን የእስልምና እምነት ተከታይ በእጅጉ አስቆጥቷል። ከአላህ ያልሆነና ሃይማኖታዊ ተልእኮ የሌለው  የጥፋት ቡድን መሆኑን የተገነዘበው ሰላም ወዳዱ ህዝበ ሙስሊምም ይህንኑ በመገንዘብ ከዳር እስከዳር በሰላማዊ ሰልፍ በግላጭ ድርጊታቸውን አውግዘው በጋራ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ። ሰላማዊ ዜጎች ለጽንፈኞች ያላቸው ምላሽም ይሄው  ከዳር እስከዳር በግልጽ እየታዩ ነው።

ድርጊቱ ከእስልምና ሃይማኖት አስተምህሮና ከህዝበ ሙስሊሙ ምግባር በእጅጉ የራቀ በመሆኑ በመላ አገሪቱ የሚገኙ የእስልምና ሃይማኖት አማኞችን  አሳዝኗል።  ጽንፈኛ ቡድኑ ከአዲስ አበባና ከሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ቀደም ሲል የመለመላቸውን አባላት በማሰባሰብ ያደረገው ሙከራ ሰላም ወዳድ ከሆነው ህዝበ ሙስሊም ነጥሎታል፤ እርቃኑንም ቀርቷል። እስልምና ሰላም ነው፤ እስልምና መቻቻል ነው፤ እስልምና መረዳዳትና መደጋገፍ መሆኑን የእምነቱ አባቶችና ምዕመናኑ ደጋግመው ይናገራሉ። እስልምን ሁከትና ብጥብጥ ነው የሚል ምንም ዓይነት አስተምህሮ እንደሌለ የእምነቱ አባቶችና ምሁራን በተለያያ አጋጣሚ ያስተምራሉ። ትክክለኛ የእምነቱ ተከታዮችም ይህንን ጠንቅቀው ያውቃሉ። መላው የእስልምና ሃይማኖት አማኞች አንድ ድምጽ ማሰማታቸውም ከዚህ የመነጨ ነው።

በተቀደሰው ሃይማኖታችን የሚቀልዱና በስማችን የሚነግዱ ጽንፈኞች ከኛ ወገን ስላይደሉ እናወግዛቸዋለንለን በሚል ድምጻቸውን አሰምተዋል።  የእስልምና ሃይማኖት አስተምህሮና እምነቱ የማይፈቅደውን ተግባር እየፈጸሙ በመሆናቸውና  ሃይማኖታችንን ለሌላ ድብቅ አጀንዳ እየተጠቀሙበት በመሆኑ በሕግ ይጠየቁልን  እያሉ ነው፡፡ እስልምና ሰላምና መቻቻልን እንጂ አመጻንና ሁከትን አያስተምርም የሚሉት አማኞቹ  ጽንፈኞቹን  ስርዓት ለማስያዝ መንግስት የሚወስደውን እርምጃ  እንደሚደግፉና ከእነሱ የሚጠበቀውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

በኦሮሚያ፣ በሶማሌ፣ በአፋር፣ በአማራ፣ በትግራይና በሌሎች ክልሎች የሚኖሩ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ሰሞኑን ባደረጓቸው ሰላማዊ ሰልፎች እንዳሰሙት ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች መቻቻልንና አብሮነትን እንጂ ጽንፈኝነትንና ሁከትን አይደግፉም፡፡ የእስልምና ሃይማኖት የአገራችንን በጎ ገጽታ ጥላሸት ለመቀባት መጠቀሚያ አይሆንም፤ የእስልምና እምነት ተከታዮችም በእንደዚህ አይነት ወራዳ ተግባር አይሳተፉም በስማችን እየነገዱ ያሉ የከሰሩ ፖለቲከኞች በመሆናቸው መንግስት መስመር ያስይዝልን ብለዋል። መላው የኢትዮጵያ ሙስሊም ሕብረተሰብ ለህዝበ ሙስሊሙ ወቅታዊ ጥያቄዎች መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ በማለት ራሱን የሰየመውን ቡድን እንደማያውቀውና ይህ በህዝበ ሙስሊሙ ስም ራሱን የሾመ አክራሪ ቡድን ህዝበ ሙስሊሙን እንደማይወክል ግልጽ መልዕክት እያስተላለፉ ነው። የህዝበ ሙስሊሙ ወቅታዊ ጥያቄ ከሌላ እምነት ተከታይ ኢትዮጵያውያን የተለየ እንዳልሆነም ተናግረዋል። ጥያቄው በአገራችን ሰላምን በማስፈን ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥና ድህነትን ድል በማድረግ ከድህነት መላቀቅ ነው። ለዚህ ደግሞ መንግስት የጀመረውን ልማት አጠናክሮ እንዲቀጥልበት ማገዝ መሆኑን አስምረውበታል። የህዝበ ሙስሊሙ ጥያቄ ሰላምና ልማት ነው።

በእስልምና ሃይማኖት ሽፋን የሚደረገውን እንቅስቃሴ እንደመልካም አጋጣሚ የወሰዱ አንዳንድ ሚዲያዎችም የገቢያቸው ማደለቢያ አማራጭ አድረገውታል። ከህዝበ ሙስሊሙ ጋር የተያያዙ የፈጠራ ዘገባዎችን በየዕለቱ እያተሙ በማሰራጨትና ብዥታንና መጠራጠርን በመፍጠር ሃላፊነት በጎደለው አካሄድ እየተጓዙ ይገኛሉ። ፈር የለቀቁና ሕገ መንግስቱን የተጻረሩ ውንጀላዎችን፣ መሰረተ ቢስ ክሶችን፣ አፍራሽ ስያሜዎች፣ ከሃይማኖት ጋር ምንም ዓይነት ተዛምዶ የሌላቸው ተግባራትን በተለያየ ጊዜ ደጋግመው በማሰራጨት ችግሩን ለማስፋትና ህዝበ ሙስሊሙ የተረጋጋ ህይወት እንዳይኖረው ለማድረግ ያልተገደበ ጥረትን አድርገዋል።

እኛ ሙስሊሞች ሀይላችን፣ ብርታታችንና ረዳታችን አላህ ነው፤ አላህ ደግሞ ሰላም፣ ፍቅርና ተስፋ ነው፡፡ በመሆኑም በሃይማኖታችን ስም የሚነግዱ አክራርያን መስመር እንዲይዙ የጀመርነውን ሰላማዊ ሰልፍ በማጠናከር በውስጣችን እንዳይሰገሰጉ ለሕግ አሳልፈን በመስጠት ድርሻችንን መወጣይ ይጠበቅብናል የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል።

መጥፎ ተግባርና ሴራ ውሎ አድሮ መጋለጡ አይቀርም። ህዝብን እያታለሉ መኖር አይቻልም። እናም ህዝበ ሙስሊሙ በሂደት የአስመሳዮች ፍላጎት የተለየ እንደሆነ በራሱ መንገድ መገንዘብ ችሏል። ከዚህ በኋላ የእስልምና ሃይማኖት ለምድን ለብሰው መንቀሳቀስ የሚያስችላቸው በር ተዘግቷል። ሁሉም ነገር ተገልጧል። ህዝበ ሙስሊሙ የቡድኖችቹን ድብቅ አጀንዳ በግላጭ ማየት ችሏል። በሕግ ሊፋረዳቸውም ተነስቷል፡፡ ለአመጽና ለሁውከት ያሰቡት ህዝብ ምላሹም ይሄው ሆኗል። ሰላም፣ ፍቅርና ተስፋን ሰንቆ ለዘመናት አዳብሮት ያለውን የመቻቻል ባህሉን ጠብቆ የመሄድ አስፈላጊነትን ከመቼውም በበለጠ ሁኔታ ተገንዝቧል። ሰላምን እንጂ አመጽንና ብጥብጥን አንሻም፤ ህዝበ ሙስሊሙ በአገሩ ደህንነት አይደራደርም፤ አገራችን ለጽንፈኞች መናኸሪያ

አትሆንም፤ ጸረ ሰላም ሃይሎች ለሕግ ይቅረቡ በማለትም ጽንፈኞች ላቀረቡለት የሁከት ጥሪ ወቅታዊ ምላሽ እየሰጠ ይገኛል።